# መድረክና የምርጫ ቅስቀሳ ስልቱ

ከሙሉታ በዳሴ

አገራችን 5ኛዋ የሆነውን አገራዊ ምርጫ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ትገኛለች። የምርጫው ግለት የጨመረ ሲሆን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችም አሉን የሚሉዋቸውን አማራጭ ሃሳቦች ወደ አደባባይ ይዘው በመውጣት ላይ ይገኛሉ።

ከነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የተባለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት ነው። መድረክ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአገራችንን የፖለቲካ ህይወት ከተቀላቀለ በኋላ እራሱን እጅግ ጠንካራ ተቃዋሚ ድርጅት ነኝ ለማለት የሚደረድራቸውን ምክንያቶችና በዚህም ሳቢያ በምርጫው ሂደት ይገባኛል የሚለውን ድል ለመቀዳጀት ያስችሉኛል በማለት የሚያሰማቸውን ማስመስገኛዎች በቅርበት ለመከታተል ሞክሬያለሁ።
በኔ እምነት መድረክ ልዩ ጉልበቶቼ ናቸው በማለት የሚኩራራባቸውንና ደጋፊዎችን ለማግባባት የሚጠቀምባቸውን እነዚህን ስልቶች በሦስት ፈርጆች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

የመጀመርያው መድረክን የመሠረቱት ሰዎች ቀደም ሲል የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር በመሆናቸው ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች በተሻለ ሁኔታ የዋነኛ ባላንጣውን የኢህአዴግን ውስጣዊ አሰራርና አስተሳሰብ ለመረዳትና ለመተንበይ ብቃት አላቸው በማለት በርካታ ድጋፍ ለማሰባሰብ የተከተለው ስልት ነው ። መድረክ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች በተሻለ በቀላሉ ለጥቃት ተጋላጭ እንዳልሆን የሚያደርግ ተጨማሪ ጉልበት ፈጥሮልኛል በማለት የሚፈክርበት ሌላው ጉዳይ እነዚህ የቀድሞ የኢህአዴግ አመራሮች በግንባሩ ውስጥ አላቸው የሚለውን ድጋፍ ነው ። በእኔ እምነት ይህ አቋማቸው መድረክን ተቀላቅለዋል የተባሉት የቀድሞ የህወሃት አባሎች እና ደጋፊዎቻቸው በገዥው ፓርቲ ጎራ ውስጥ ጥምረቱን ከማንኛውም አይነት ጥቃት ለመታደግ የሚችል ጠንካራ ተቃውሞን መቆስቆሳቸው አይቀርም ወደሚል የተሳሳተ ግምትም ሳያመራቸው እንዳልቀረ እጠረጥራለሁ። ገዥው ፓርቲ መድረክን ለተቀላቀሉት የቀድሞ ህወሃቶች አሁንም ድረስ በተለያየ መንገድ ድጋፋቸውን ይቸራሉ የሚባሉትን አባሎቹንና ደጋፊዎቹን ላለማስቀየም በቅንጅቶች ላይ የወሰደውን አይነት እርምጃ በመድረክ ላይ ላይወስድ ይችላል በሚል ስሌት ላይ የተገነባ እምነት በመድረኮች ሰፈር ሰፍኗል። ይህን ለማለት ያስቻሉኝንና በመድረክ ውስጥ የታዩ የሁከትና የረብሻ ዝንባሌዎች ወደ ኋላ በዝርዝር ለማሳየት እሞክራለሁ ።

ሁለተኛው መድረኮች እንደ 97ቱ ቅንጅት በብሄራዊ ትምክህተኝነት ጥርጣሬ ውስጥ ከመውደቅ ይታደገናልና ብርቱ ጥንካሬያችንም ነው በማለት የሚያነሱት ስብስቡ አገራዊና ብሄራዊ ድርጅቶችን ያካተተ ጥምረት መሆኑን ነው። መድረኮች የመድረክ አባላት የሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶች ጥምረቱን ለመፍጠር የተከተሉት መንገድ ከዓመት በላይ የወሰደ መሆኑንም እንደሌላ የጥንካሬያቸው ማሳያ ይጠቅሱታል።

ሶስተኛው መድረኮች ገዥው ፓርቲ ከእነርሱ ጋር በንፅፅር ሲታይ ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓትና በተለይ ደግሞ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ልባዊ ፍላጐትም ሆነ ይህን እውን ለማድረግ የሚያስችል የፖለቲካ ፕሮግራም የለውም በማለት የሚያቀርቡት ስሞታ ነው። መድረኮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚያሰሙትን ይህን ስሞታ ዓለም አቀፍ ማኀበረሰቡ ለሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት የቸረውን እውቅና ለማሥሰረዝ እንዲሁም ስርአቱን አስመልክቶ በኀብረተሰቡ ዘንድ ጨለምተኝነትንና ተስፋ ቆራጭነትን ለማስፋፋት እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚሞክሩ ኋላ ላይ በዝርዝር ለማሳየት እሞክራለሁ።
በመጀመሪያ ግን እስቲ ከላይ የተመለከቱትን የመድረኩ "የጥንካሬ" ቁመናዎች ፋይዳ በቅርበት እንመልከት።

## 1. የቀድሞ የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች ለመድረኩ ተጨማሪ ጉልበት ናቸውን?

እርግጥ ነው መጀመሪያ በግለሰብ ደረጃ በኋላ ደግሞ በአንድነት በኩል በመድረክ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት አቶ ስዬ አብረሃ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ ገብሩ አስራት ቀደም ባሉ ግዜያት የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር አባላት እንደነበሩ ይታወቃል ። እነዚህ ሶስት ግለሰቦች በህወሀት ውስጥ አቆጥቁጦ ጠቅላላ ግንባሩን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ከትቶት በነበረውና በ1993 ዓ.ም. ተከስቶ በነበረው ክፍፍል ሳቢያ ከድርጅቱ በተባረረው የአንጃ ቡድን ውስጥ በነበራቸው ተሳትፎ ከኢህአዴግ ተባርረው የወጡ ግለሰቦችም ናቸው ። በበኩሌ የእነዚህ ግለሰቦች መድረክን መቀላቀል ለሰብሰቡ ተጨማሪ ጉልበት መሆኑን በሚመለከት ከተሰጡ ማብራሪያዎች ሁሉ ለመድረኩ የነበራትን ውግንና ለመሸፈን ሞክራ በማታውቀው በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ከቀረበው ማብራሪያ የተሻለ በጣም ግልፅና የተፍታታ ሀተታ አላጋጠመኝም። ጋዜጣዋ ከላይ እነዚህ የኢህአዴግ የቀድሞ ከፍተኛ አመራር የነበሩ ግለሰቦች ምክንያት መድረክ ሁለት ፖለቲካዊ ድሎችን እንደሚጐናፀፍ በተለያየ ወቅት ባቀረበቻቸው ዘገባዎቿ አመልክታ ነበር።

እነዚህም፦

ሀ) እነ ስዬ የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ስለነበሩ ኢህአዴግን ከእግር እስከ ራሱ ያውቁታል። ጠላትን ማወቅ ግማሽ ድል ነውና ኢህአዴግን በደንብ የሚያውቀው መድረክ በፖለቲካ እንቅስቃሴው የባላንጣውን ስልቶች አስቀድሞ ስለሚረዳ ከሌሎች ተቃዋሚዎች በተሻለ ለድል የቀረበ እድል ይኖረዋል።

ለ) እነ ስዬ በኢህአዴግ ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ደጋፊዎች ስላሏቸው ኢህአዴግ ''በ1997 ዓ.ም. በቅንጅት ላይ የወሰደውን ዓይነት የመላ አባላቱን ድጋፍ የሚያገኝ እርምጃ በመድረክ ላይ ለመውሰድ ያዳግተዋል።

እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ተጨባጭ እውነታ አላቸውን ? ለጥምረቱ አስተማማኝ ጥንካሬ በማጎናፀፍ ለመድረክ አባላት አስተማማኝ የድል ዋስትና ያስገኙላቸዋልን? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል።

በእርግጥ እንደተባለው እነ ስዬ የህውሃት መስራቾች እና ከፍተኛ አመራሮች ነበሩ። በዚህም ምክንያት እስከነበሩበት ግዜ ስለነበረው ኢህአዴግ የሚያውቁት ብዙ ነገር ሊኖርም ይችላል ። ነገር ግን በአንድ ወቅት የግንባሩ አንጋፋ አመራር አባል መሆናቸው በራሱ በኢህአዴግ ውስጥና በደጋፊዎቹ ዘንድ የነበራቸውን ከበሬታና ተቀባይነት ይዘው ለመዝለቃቸው ዋስትና ይሆናል ወይ ? የድርጅቱ ቁመናስ ከመውጣታቸው በፊት ከነበረው ሁኔታ ብዙም ያልተለየ ነውን ? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው ተገቢ ነው ። ለጥያቄዎቹ የሚሰጠው ምላሽ አዎንታዊ ከሆነ በርግጥም መድረኮች የድል ዋስትናባይሆንም እንኳ አንድ የተሻለ ጉልበት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል የሚለውን ግምት ማላመጥ እንችል ይሆናል ።ምላሹ አሉታዊ ሆኖ ከተገኘ ግን ይህ የጉልበት ልፊፋ ባዶ ቀረርቶ ወይም ዴማጎጊ ሆኖ መቅረቱ ነው ። ፋከራው የእውነት መሰረት ይኑረውም አይኑረውም የመድረኩን አደገኛ የትግል አቅጣጫ እንዴት አመላካች እንደሆነም ወደ ኋላ ለማሳየትም እሞክራለሁ። በቅድሚያ ግን እነ ስዬ እንደተባለው በኢህአዴግ ጎራ የሚገኝ በርካታ ደጋፊ አላቸው የሚለውን አባባል እውነተኛነት እስቲ እንፈትሽ ።

ለጉዳዩ ትኩረት የሰጠ ማንም ሰው የእነስዬን የህወሀት መስራችነትና የቆየ የትግል ገድል መነሻ በማድረግ የሚቀርበው ትንተና ሳይገልፅ የሚያልፈው አንድ ግዙፍ ሀቅ መኖሩን ማስተዋል አያዳግተውም ። ይሄውም ሰዎቹ ድርጅቱን ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ከትቶት የነበረውን የአንጃ እንቅስቃሴ የመሩና በድርጅቱ ውስጥ በተደረገው ውስጣዊ ትግል ሙሉ በሙሉ ተሸናፊ ሆነው ከድርጅቱ የተባረሩ መሆናቸው ነው። እነዚህ ሰዎች በመላ ድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ፊት ክብርና ሞገሳቸውን ተገፈው ከድርጅቱ የተሰናበቱ የመሆናቸውን እውነታ መድረኮች በዝምታ ለማለፍ ይሻሉ። የ1993ቱ የውስጠ ድርጅት ትግል እነ ስዬ በኢህአዴግ ውስጥ አቆጥቁጦ ድርጅቱን ለከፋ ዝቅጠት ዳርጎት የነበረውን የፀረ ዴሞክራሲየዊ፣ የትምክህት እና የንቅዘት ዝንባሌ መወከላቸው ለመላ የግንባሩ አባል ድርጅቶችና ደጋፊዎች ማረጋገጡን የስዬ ወለድ ጉልበት አቀንቃኞች ማንሳት አይፈልጉም ።

እውነታው ሰዎቹ ለመድረኩ ያመጡለታል የተባለውን ጥንካሬ ከንቱ ቅዠት ስለሚያደርገው መድረኮች ይህን እውነታ አድበስብሰው በዝምታ ማለፍን የመረጡ ይመስለኛል።

የእነስዬ አንጃ ኢህአዴግንና አባል ድርጅቱን ህወሃትን ከፍተኛ ቀውስና ዝቅጠት ውስጥ የሚዘፍቅ በአብላጫዎቹ እይታ የበሰበሰ አስተሳሰብን መወከሉ ተረጋግጦ ርዕዮተ ዓላማዊና ፖለቲካዊ ሽንፈትን የቀመሰ የጥቂት ሰዎች ስብስብ እንደነበር ይታወሳል። በድርጅቱ ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ እመርታን ያስከተለው የአብላጫው አስተሳሰብ ሀገሪቷን ከመበታተን ይታደጋል በማለት ይዞት የተነሳውን የዲሞክራሲና የልማት አጀንዳ በመፃረር የተመሰረተው የእነስዬ አንጃ በድርጅቱ ውስጥ እያቆጠቆጡ የመጡ የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን ሰፊውን ህዝብም ሳይቀር ያስቀየሙ አጉል አሰራሮችንና ዝንባሌዎችን የሚወከል መሆኑ ተረጋግጧል ። የአብላጫውን የተሃድሶ እንቅስቃሴ ለማሰናከል ያራምድ በነበረው አቋም የተነሳም የመላ አባላቱን ፖለቲካዊ ድጋፍ ለማጣት ተዳርጓል ። ድርጅቱ ከታገለለት አላማ ጋር ተፃራሪ የነበረው የእነ ስዬ ትምክህተኛ አንጃ በፈፀማቸው አሳፋሪ የስስትና የሙስና ተግባራት የመላ ትግራይ ህዝብን ድጋፍ አሳጥቶታል ። ይህ የተድበሰበሰ እውነታ እነስዬ አሁንም በኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎቹ ዘንድ ድጋፍና ተቀባይነት አላቸው የሚለውን የመድረኮች ማግባቢያ የማይጨበጥ ባዶ ቅዠት መሆኑን ያመለክታል።

የእነስዬ አንጃ በሽንፈት ከድርጅቱ ከተባረረ በኋላ በተሃድሶው እንቅስቃሴ የተጠናከረው ኢህአዴግና አባል ድርጅቱ ህወሃት ከቀውሱ በፊት ከነበረው ቁመና በእጅጉ የተለየ መሆኑ አያጠያይቅም። በሌላ አባባል እነ ስዬ የሚያውቁት ድርጅት ተሃድሶ የሚያስፈልገው እና እራሱን በአዳዲስ ሃሳቦች ማጥለቅለቅ የነበረበት ድርጅት ነበር። በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ ከ1993 ዓ.ም. በኋላ ከፍተኛ የሆነ የተሃድሶ ፕሮግራም ነድፎ ይህንኑ ተግባር ላይ አውሎታል። በውጤቱም ጥቂት አባላት የነበሩት ኢህአዴግ 4.5 ሚሊዮን አባላት ወደ አሉት ትልቅ ድርጅትነት ራሱን ቀይሯል። ድርጅቱ የማያቋርጥ የለውጥና የተሃድሶ ፕሮግራም እንዳለውም በአስተማማኝ መልኩ አረጋግጧል።እንኳንስ ርእዮተ አለማዊ ኮምፓሱን የጣለ እነ ስዬነ የመሰለ ሰው ቀርቶ የድርጅቱን እምነቶችም እንኳየሚጋራና ከ1993 በፊት ኢህአዴግን የሚያውቅ ሰው አሁን መልሶ ቢያየው በአዳጊ ቅስቃሴው ሳብያ ድርጅቱን ማወቅ እንደሚሳነው እሙን ነው። ትተውት ከሄዱበት ቦታ ተቸክሎ የቀረ ይመስል ገና ድሮ የሳይንሳዊ ርእዮተ አለም ማተባቸውን የበጠሱት የእነስዬ ተሞክሮ አንዳች ተአምር ያስከትላሉ ብሎ መስበክ እራስን ማታለል ይመስለኛል።

*ለዚህም ሁነኛ ማሳያ የሚሆነው መድረክ የምርጫ ስነ-ምግባር ደንቡን በተመለከተ እየተከተለ ያለው ስልት ነው። አቶ ስዬ አዲስ ነገር ላይ ያስነበቡን ፅሁፍ የሚያሳየው መድረክ የሥነ ምግባር ደንቡን አስመልክቶ የተከተለው ስልት በሴራ ትንታኔ (conspiracy theory) የታጨቀ ኢህአዴግን እንደ ፖለቲካ ባላንጣ ሳይሆን የተንኮል መፈልፈያ ማሽን አድርጎ የሚስል ነው። ነገር ግን መሬት ላይ ያለውን ሐቅ ግን የሚያሳየው ተቃራኒውን ነው። ኢህአዴግ የምርጫ ሥነ ምግባር ደንቡን በሚመለከት የተከተለው ስልት አወንታዊ ሃሳቦችን መሰረት ያደረገ የreal politic አስተሳሰብ ነው።*

*ኢህአዴግን ያውቁታልና የፖለቲካ ትርፍ ያስገኙሉናል ተብለው የንጉስ አቀባበል የተደረገላቸው የእነ ስዬ አብርሃ አመራር በስነ ምግባር ደንቡ የድርድር ሂደት ውስጥ ለመድረኩ ያተረፈው ነገር ቢኖር ጥምረቱ በሂደቱ ውስጥ ቢሳተፍ ኖሮ በሃገር ውስጥና በአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ፊት ሊያገኝ ይችል የነበረውን ሞገስ እና ይሁንታ በማሳጣት መድረኩን ለከፋ የፖለቲካ ኪሳራ መዳረግ ነው ። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ መድረኩ ለዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ትግል ያለውን ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ውስጥ የከተቱ ተለዋዋጭ አቋሞችን እንዲይዝ ማድረጋቸው ብዙ የተወራለት የአመራር ብቃታቸውን ለትዝብት ዳርጎታል ። አመራሩ መድረክን ከሌሎች የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋርም ቀጥተኛ ግጭት ውስጥ ነው የከተተው ። በዚህ የድርድር ሂደት ተአምር ይፈጥራል የተባለለት የእነ ስዬ አመራር ከተሃድሶው ወዲህ እንኳ ባበበጀውና በየግዜው በሚሰፋና በሚጠናከር ህዝባዊ ግንኙነቱ ፣ በስኬት ከመኩራራትና ከመታበይ በሚያስጥለው የማያቋርጥ የግምገማ ባህሉ ፣ በተዋረድ በአመራሩ ውስጥ በሚታየው የማይነጥፍ የአዲስ ሃሳብ አመንጪነት እና ህያው ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ባህሉ የተነሳ በየግዜው አዳጊ የሆነውን ኢህአዴግን እንደእጁ መዳፍ የማያውቀውና ሊያውቀውም የማይችል መሆኑን አሳይቷል።*

*በእኔ እምነት የኢህአደግ የፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ስኬቶች እርስ በርስ ተመጋጋቢ ከሆኑ የጠንካራ ርእዮተ አለም መሰረት ያላቸው ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳቦች እና ከተግባራዊ ተሞክሮዎች የተገኙ ግንዛቤዎችና እውቀቶች ውጤት አንጂ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ድግምት የጫነች አህያ ምትሃታዊ ውጤቶች አይደሉም ። የፖለቲካዊ ስኬቶች እና ትንበያዎች ትክክለኛነት የሚወሰነው ከሌሎቸ ነገሮች በተጨማሪ ተንታኙ አካል በተጨባጭ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ ባለው ትክክለኛና ግንዛቤ ፣ በፖለቲካ ሃይሎች አሰላለፍ ፣የማህበራዊ መሰረታቸው መነሻ በሆኑ ልዩ ልዩ ጥቅሞች አና ፍላጎቶች ላይ ባለው ሳይንሳዊ እና ትክክለኛ አረዳድ እና ግንኙነታቸውን የሚወስኑ ህግጋትን ለመረዳት ባለው የግንዛቤ ብቃት ላይ ነው። ይህ የትንተና እና የግምገማ ብቃት ደግሞ ዞሮ ዞሮ ከተንታኙ ርእዮተ አለማዊ አቋም ተነጥሎ ብቻውን የሚቆም ነገር አይዶለም። ስለሆነም የነባራዊው የተለዋዋጩ የፖለቲካዊ ሃይሎች አሰላለፍ እውቀት ለጥቂት የበቁ initiated ግለሰቦች በፀጋ የተገለጠ አንዳች ምስጢራዊ ጥበብ esoteric knowledge እንደሆነ አድርጎ ለማሳየት መሞከር ወይ በቅንነት ከተነሳ የዋህነትን አሊያም ደግሞ ፖለቲካዊ ቁጭ በሉነትን ከማሳየት ያለፈ ትረጉም ይኖረዋል የሚል እምነት የለኝም ።*

*የኢህአዴግን ድርጅታዊ ባህል የማያውቁ ሰዎችን ለማማለል ታስቦ የሚራገበው ሌላው መሰረተ ቢስ ወሬ በእነዚህ የቀድሞ ኢህአደጎች ላይ ተገንብቷል የሚባለው የተክለ ስብእና አምልኮ ነው። ኢህአዴግ ውስጥ ግለሰቦች አገሪቷን ካለችበት የድህነት አረንቋ ለማውጣት የሚያገለግሉ ድልድዮች እንጂ በራሳቸው ፋይዳ የሚሰጣቸው እይደለም። ለዚህም ነው የኢህአዴግ መሪዎች በስማቸው የማይዘፈንላቸው። መሪዎቹ በድርጅቱ ውስጥ ሳሉ የሚያፈሩት ከበሬታ (ቃሉ በኢህአደግ መዝገበ ቃላት ውስጥ የሚገኝ ስላልመሰለኝ መታፈርን*

*ትቼዋለሁ ) ለቆሙለት አላማ ካላቸው ፅንአት ጥንካሬና ብስለትና ጋር የተቆራኘ እና የማይነጣጠል ነገር እንጂ የተክለ ሰብእናቸው ትልቅነት ውጤት አይደለም። ስለሆነም በኢህአዴግ ውስጥ አሉ የተባሉት ደጋፊዎች እነስዬ የቀድሞ ቅንጅትን ፈለግ ቢከተሉም እንኳ ከተጠያቂነት የሚያስጥሉዋቸው ሃያል ደጀኖች ናቸው የሚለው መድረኮች ውስጥ የሰፈነው አስተሳሰብ የግንባሩን ድርጅታዊ ባህል እና እውነታውን የማይወክል ጨርሶ የተሳሳተ አመለካከት ነው ።*

*በኢህአዴግ አባላት እና በአመራሩ መሃል የተኮተኮተው የወንድማማችነትና የትግል አጋርነት መንፈስ መሰረቱም ምንጩም የአላማ አንድነት እንጂ የግለሰቦች ተክለ ሰብእና ባለመሆኑ እነ ስዬ በመስመር ልዩነት ከየአባል ድርጅቱ ሲባረሩ ከዚህ ቀደም በኢህአዴግ አባላት ተችሯቸው ከነበረው አክብሮት ጋርም እስከናካቴው ተለያይተዋል ።*

*ስለሆነም መድረክ በእነስዬ አማካይነት ከኢህአዴግ ካምፕ የሚታፈስ የቆረጣ ድጋፍ ለማግኘት አቅዶ ከሆነ ወይም እነ ስዬ እንዲህ አይነቱን የተስፋ ምግብ በገፀ በረከትነት ለመድረክ አቅርበው ከሆነ ነገሩ ከህልም እንጀራነት የዘለለ ውጤት እንደማይኖረው እሙን ነው ።*

*በአሁኑ ወቅት በኢህአዴግ ውስጥ የአንጀኝነት ፖለቲካም ሆነ የእነስዬም ጉዳይ በማይቀለበስ ሁኔታ ግብአት መሬት ገብቷል። ስለዚህ መድረኮች ሊገነዘቡት የሚገባ አንድ አብይ ቁምነገር ቢኖር ኢህአዴግ በታሪክ የማይቆምር ፣ ሰዎች ዱሮ የነበራቸውን አስተዋጽኦ ተሸክሞም ትዝታ ወስጥ ሰምጦ የሚያንጎላች ድርጅት አለመሆኑንና የግለሰብ አባላቱን ፋይዳም የሚመዝነው እዚህና አሁን (in the hear and now) ባላቸው አቋምና አስተዋጽኦ መሆኑን ነው ።*

*ይህ የመድረኮች ከንቱ የአቅም ፋከራ በዚህ አቋም አቀንቃኞች በከፊል የተሸሸገ አንድ ያደባ አደገኛ አዝመዘሚያ መኖሩን ያመለክታል። አልመታህም ከ ዛፍ ላይ ውረድ ቢለው አልመታህምን ምን አመጣው አለ እንደሚባለው በዚህ የቅዥትም ሆነ እውን የአቅም ፋከራ ውስጥ በቀድሞው ቅንጅት ላይ የተወሰደው አይነት እርምጃ እኛ ዘንድ አይሰራም የሚለው ቀረርቶ ተመሳሳይ የቀለም አብዮት የማስነሳት ውጥን መድረኮች ውስጥ መኖሩን አመልካች ነው ። ይህ ሆነ ተብሎ እይተሰራጨ ያለ ቀረርቶ ካለፈው ተሞክሮ ልምድ ለመማር ፈቃደኝነቱ ለጎደላቸውና የሃይልና የአመፅ አማራጭን ሲያላምጡ ለሚታዩ በስብስቡ ውስጥ ላሉ ሃይሎች መድረኩን በተቀላቀሉት በእነስዬ አይዟችሁ አለንላችሁ ለማለት የቀረበ የእጅ መንሻ ገፀበረከት ነው የሚል እምነት አለኝ ።*

## 2. <u>*መድረክና የአዲስ ሃሳብ አመንጭነት*</u>

*መድረክ የኢትየጵያን ፖለቲካ ከተቀላቀለ በኋላ በሶስት መልኩ አዳዲስ ነገሮችን ይዥ መጥቻለሁ በማለት ላይ ይገኛል። እነዚህም፥-*

- መድረክን የፈጠሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከአንድ ዓመት በላይ ውይይት ማድረጋቸው
- አዳዲስ ኃሳባትን የያዛ ማኒፌስቶ ማዘጋጀቱ እና
- አዲስ የትግል ስልት እከተላለሁ ማለቱ ናቸው። ምንም እንኳ ከላይ በተገለፀው መልኩ መድረክ ወደ ኡትዮጵያ ፖለቲካ ሶስት አዳዲስ ነገሮችን ይዤ መጥቻለሁ ቢልም በእኔ እምነት ግን መድረክ የሚከተላቸው ስልቶች አዲስ ያልሆኑ በተግባር ተፈትነው አከሳሪ የሆኑ የቅንጅት እና የአንጃ ስልቶችን ያዳቀለ ነው።

ከመነሻውም የማይገናኝ የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸው ፓርቲዎች የአላማ ሽግሽግ ለማድረግ ያውም በተራራቀ ጊዜ በሚደረግ ስብሰባ በአንድ ዓመት ጊዜ ውሰጥ መድረክ የተሰኘ የፖለቲካ ቅንጅት ፈጥረናል ቢሉ አይገርምም። ነገር ግን የመድረክ አባላት በሆኑት ፓርቲዎች መካከል ያለውን የፕሮግራም ልዩነት በደንብ ላጤነ ሰው ልዩነቱ ከማንኛውም የፖለቲካ ቅንጅት ስሌት አንፃር ሲታይ በ10ዓመት የማይሸጋሽግ መሆኑን ግልፅ ይሆንለታል ። የመድረክ ስብስብ ለ1 ዓመት ያህል በፖለቲካ ድርጅቶች መሃከል የተደረገ ምክክር ውጤት መሆኑ በራሱ ምንም አይነት ኦሪጅናሊቲን አያመለክትም ። ምክንያቱም ከዚህ በፊት በአገሪቱ ውስጥ ከተፈጠሩት ሌሎች የፖለቲካ ቅንጅቶች ይለየኛል የሚለው ስብስቡን ለመፍጠር በፈጀው ግዜ እንጂ በሌላ መሰረታዊ ቁም ነገር አይደለምና ነው።

ሌላው መድረክ ለኢትዮጵየ ፖለቲካ አምጥቸዋለሁ የሚለው አዲስ ነገር ማኒፌስቶው ነው። ማኒፌስቶውን በደንብ አድርጌ አንብቤ እንደተረዳሁት ቅንጅት በ1997 ዓ.ም. ካዘጋጀው ማኒፌስቶ የተቀዱ ሃሳቦችን በውስጡ ያከተተ የኢህአዴግ ፕሮግራሞች ላይ የተዘረዘሩተን መረሆዎችና ግቦች በየተራ ለማጣፋት ሲባል የተከ ሸኑ በራሳቸው የማይቆሙ ድሪቶ ሃሳቦችን የካተተ ማንፌስቶ ነው። ከተለያዩ ድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራሞች የተወሰዱትና የቅጂ መብት ውዝግብ ማስነሳት የጀመሩትን እነዚህን የማኒፌስቶው ቅይጥ ሃሳቦች እንደ ኦሪጅናል ስራ ኳኩሎ ማቅረባቸው በአመቱ ምርጥ ኮሜዲያንነት የሚያሸልማቸው ይመስለኛል።

መድረክ በሶስተኛ ደረጀ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ፋና ወጊ ሆኜበታለሁ ያለበት ሌላው ጉዳይ ኦሪጅናል ነው የሚለውን የትግል ስልቱን ነው። በእኔ እምነት መድረክ የሚከተለው የትግል ስልት በ1993 ከኢህአዴግ የወጡት አንጃዎች እና በምርጫ 97 ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ የተከተለውን የመታገያ ስልት ያዳቀለ የትግል ስልትነው። መድረከ የመታገያ ስልት ከቀድሞው የህወሃት አንጃ እና ከቅንጅት ጋር እንደምን እንደሚመሣሠል ለማየት እንሞክር ።

## ሀ) የቅንጅት እና የመድረክ መመሣሠል

### 1. ያልተቀናጀ ቅንጅት

በ1997 ምርጫ የቀድሞው ቅንጅት በፕሮግራም ላይ የተመሰረተ ኪዳን ሳይሆን የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው የሚለው አንድ የጋራ አካፋይ አቋም ያሰባሰባቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ ነበር ። ቅንጅት በተባለው ጥምረት ወስጥ የተሳተፉት ፓርቲዎች የወል የፖለቲካ ዓላማ ኢህአዴግን ከሥልጣን የማስወገድ አጀንዳ ብቻ ነበር።

በመሆኑም ቅንጅት በጋራ የሚያታግል የወል ሥነ ልቦናዊ ፣ የፖለቲካዊና ሞራላዊ ዝግጅት ባልነበራቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ የተፈጠረ ውህደት ነበር። በዚህም ምክንያት ቅንጅት ወደ ሰባት የተለያዩ ፓርቲዎች የተሰነጣጠቀ የፖለቱካ ስብስብ ለመሆን በቅቷል። በተመሣሣይም የመድረክ መስራች አባላት በሆኑ አንዳንድ

*ድርጅቶች እንጋፉ አባላት አመራሮች ዘንድ ድርጅታቸው መድረክን መቀላቀሉን የሚቃወም የሃሳብ ልዩነት ተንፀባርቋል። ከዚህ አንፃር አንዳንዶቹ መድረክን የፈጠሩ ፓርቲዎች መድረክ የሚባለውን ጥምረት ለውስጣዊ ችግሮቻቸው ማናጠብያ አድርገው መጠቀማቸውን እንጂ መድረኩ ባዘጋጀው የፖለቲካ ፕሮግራም ዙሪያ የጠራ አቋም ወስደው አለመቀላቀላቸውን የሚያሳዩ በርካታ አብነቶችን ማንሳት ይቻላል። ለምሣሌ የመድረክን የትግል ስልት አስመልክቶ ሊቀመንበሩ ዶ/ር መረራ ጉዲና የኬንያን እና የዙንባብዌን ሞዴል እንከተላለን ሲሉ ሌሎቹ አመራሮች ግን በአደባባይ ይህን ማውገዛቸው በአመራሩ መሀከል የሚታየውን የአቅጣጫ ብዥታ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ። ስለሆነም መድረክ ከቅንጅት በባሰ ሁኔተ ያልተቀናጀ የፖለቲካ ስብስብ ነው ማለት ይቻላል ።*

## *2. የተለያየ ፕሮግራም ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት*

*በ1997 ዓ.ም. ምርጫ እንዳስተዋልነው ቅንጅት ለመፍረሱ አንዱ ምክንያት ፓርቲዎቹ ተጣራሽ የፖለቲካ ፕሮግራሞችና አቅጣጫዎች የነበሯቸው በመሆኑ ነው። ለምሳሌ ቀስተደመና የፖለቲካ ፕሮግራም በሶሻል ዲሞክራሲ ርእዮትን አቀነቅናለሁ ሲል ኢዴፓ ደግሞ ሊበራል ፖለቲካዊ ፕሮግራም ነበረው።*

*በዚህም ምክንየት ቅንጅት ብዙ ሳይራመድ ወደ ትንንሽና ስብርባሪ ፓርቲዎች ተቀይሯል። ይህም የተለያየ የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ቅንጅት ሥር ሊሰሩ እንደማይችሉ ያሳያል። በተመሣሣይም መድረክን የመሠረቱት ፓርቲዎች ፍፁም ተቃራኒ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራምን የሚከተሉ ናቸው። ለምሳኔ አረና ሊብራሊዝምን ሲከተል የደቡብ ህብረት ደግሞ ሶሻል ዴሞክራሲን ይመርጣል። አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ አገራዊ ፓርቲ ሲሆን ብዙዎቹ ፓርቲዎች ደግሞ ብሔርን መሠረት ያደረገ የፖለቱካ አደርጃጀት የተከተሉ ናቸው። መድረክ ኢትዮጵየ ውስጥ ጠንካራ የፖለትካ ድርጅት ነኝ የሚለው በውስጡ እንዲህ መሰል የፕሮግራም ተቃርኖዎችን ተሸክሞ ነው። በእኔ እምነት የመድረክ እጣ ፈንታ እንደ 97ቱ ቅንጅት ወደ ትናንሽ ስብርባሪ ፓርቲዎች መቀየር መሆኑን ለማወቅ ነብይ መሆንን አይጠይቅም ።*

## *3. በዲያስፖራ እና በውጭ አገር ዲፕሎማቶች የመተማመን አባዜ*

*ቅንጅት በ1997 ዓ.ም. እንደታየው እጃቸው ረጅም በሆኑ ዲያስፖራዎች ፍላጐት እና ምኞት ስር የተቋቋመ ፓርቲ ነበር። በዚህ ምክንያት ቅንጅት በራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም መመራት እና የፖለቲካ ኳሱን አገር ወስጥ ወደሚኖረው ህዝብ መለጋት ተስኖት ነበር። በአጭሩ ዲያስፖራዎች በሚሰጡት ገንዘብ ልክ እንዳሻቸው የሚያስከረክሩት የፖለቲካ ስብስብ ነበር።*

*በተመሣሣይም የቅንጅት አመራሮች የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው የኢዮጵያ ህዝብ ጋር ከመመካከር ይልቅ ወደ ዲፕሎማቶች ወይንም ወደ ዲያስፖራው መሮጥ የሚቀላቸው እና የዲፕሎማቶቹን ይሁንታ ማግኘት ኢትዮጵያ ውሰጥ በትረ ስልጣን ለመጨበጥ የሚያስችል መንገድ አድረገው የሚቆጥሩ ነበሩ።*

*መድረክም በአሁኑ ወቅት ልክ እንደ ቀድሞው ቅንጅት የዲያስፖራ ወኪል ሆኖ እየሰራ ያለ የፖለቲካ ድርጅት ነው።*

በተግባር እንደታየው መድረክ  የሚመራው እና የትግል ስልቱንም የሚነድፈው ከእራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ  ተመስርቶ ሳይሆን  አይኑን ከፍተኛ የመዋጮ ገንዘብ ምንጭ ከሆነው ዲያስፖራ ላይ በመጣል ይህን ክፍል ከልብ ማስደሰትን ግቡ አድርጎ በመንቀሳቀስ ነው ።

በተመሣሣይም የመድረክ አመራሮች ማንኛውም የፖለቲካ ጉዳይ ወደውጭ ዲፕሎማቶች ይዘው የሚሮጡ እና ከህዝቡ በላይ ዲፕሎማቶችን እና የአለም አቀፍ ማህበረሰብን መራጫቸው (constituency) አድርገው የሚወስዱ  ናቸው። ለዚህም አቶ ስዬ << ስነ ምግባር ሲሉ>> በተሰኘው ጽሑፋቸው ለቀጣዩ ምርጫ  ስኬት  የፕሬዚዳንት ኦባማን ጣልቃ ገብነት መማፀናቸው እና አለም አቀፍ ማህበረሰቡ ጣልቃ ይገባ ዘንድ አቤቱታ ማቅረባቸው በአስረጅነት ሊጠቀስ ይችላል ። እዚህ ላይ  መረሳት የሌለበት ጉዳይ አቶ ስዬ ፕሬዘዳንት ኦባማ  ጣልቃ ካልገቡ በአገሪቱ ውስጥና በክፍለ አህጉሩ ውስጥም ሊከሰት ይችላለል በማለት የጠቀሱት ሁከትና አለመረጋጋት በመድረኩ ውስጥ ቀጣዩን ምርጫ ለማወክ የተጠነሰሰውን አደገኛ የሁከትና የብጥብጥ እርሾ  አመላካች ነው።ከሁሉም በላይ እነ አቶ ስዬ የወጠኑት ሁከትና ረብሻ በመጠኑ አነስተኛ ያልሆንና የውጭ መንግስታት ጣልቃ ገብነትን ያህል እርምጃ የሚጠይቅ ከባድና አደገኛ ነውጥ መሆኑን ከወዲሁ አመላካች ነው ።

## ለ) የመድረክና የ1993ቱ የህውሐት አንጃ መመሳሰል

### 1. የሽሽት ፖለቲካ

በ1993 እንደታየው የህውሐት አንጃ ከአብዛኛው የድርጅቱ አመራር ጋር ስለነበረው የልዩነት ነጥብ የህወሓት አባላትን ለማስረዳት በመቀሌ ተዘጋጅቶ በነበረው የካድሬዎች ስብሰባ በተሰውት ታጋዬችና በህውሐት ባንዲራ ጭምር ቢለመኑም እንኳ የተዘጋጀው መድረክን ረግጠው ወጥተዋል። በእነ ስዬ ተፅእኖ መድረክም ይህን የሽሽት ፖለቲካ የመረጠ ይመስላል ። በስነ ምግባር ድርድሩ እንዲሳተፍ የቀረበለትን ተደጋጋሚ ግብዣ አሻፈረኝ በማለት አንጃዊውን   የሽሽት ስልት አጥብቆ መከተሉን  አሳይቷል።  አቶ ስዬ ይህን የአንጃ የሽሽት ፖለቲካ መድረክ ውስጥ ሲያስተዋውቁ የመጨረሻ መዘዙንም አብረው አለማሳየታቸው ከወዲሁ ግልፅ እየሆነ ነው ። እርሰቸውን ለሽንፈት ያበቃው ስልት መድረክ ቤት ሲገባ አዲስ  ምትሃታዊ ሃይል የሚቀዳጅ አይመስለኝም ።

### 2. እራስን እግዝሮ የማየት በሽታ

ህወሓት በኢዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የመካከለኛ ሰው እድሜ ቆይታን ያደረገ ድርጅት ነው።  ከዚህም በበለጠ ከሚወክለው የትግራይ ህዝብ ጋር ጠንካራ የሆነ የሞራል፣ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የኢኮኖሚና የታሪክ ትስስር ያለው ድርጅት ነው። ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ግን እራስን አግዝሮ በማየት ደዌ የተጠቃው የ1993ቱ አንጃ በተለይም ራሳቸውን ሰማይ የሰቀሉት አቶ ስየ አብርሃ የፖለቲካ እጣ ፈንታቸውን  ከጠቅላላው  የትግራይ ህዝብ እጣ ፈንታ ጋር በማስተሳሰር  እኛ ከሌለን ትግራይ የለችም፣ ህወሓትም ይፈርሳል የሚል አቋም ይዘው ነበር ። በዚህ ለራስ የተሰጠ ከንቱ ውዳሴ ታወሩና ህዝቡ ተው፣ በጊዜ ታረሙ፣ ከጥፋት ድርጊታችሁ ተመለሱ ሲላቸው አሻፈረኝ አሉ። እጣ ፈንታቸውም ውድቀት ሆነ። አሁንም መድረክ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስለማይመጥኑኝ ከእነሱ ጋር በድርድር አልሳተፍም፣ እኔ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ትልቁና ወሳኙ ፓርቲ ነኝ እያለ በአደባባይ ቀረርቶ ማሰማቱ በአንጃው ልክፍት ለመጠቀቱ  ሁነኛ ማሳያ ነው።

## 3. *ገዥው ፓርቲ ለዲሞክራሲ ያለውን ቁርጠኝነት በሕዝቡና በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዘንድ ጥርጣሪ ውስጥ ማስገባት*

*ገዥው ፓርቲ ለዴሞክራሲ ያለውን ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ መድረክ ያለ የሌለ የሰው ኃይሉንና ገንዘቡን አሟጦ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ገዥው ፓርቲ ለዴሞክራሲ እንዳልቆመ አድርጎ በማቅረብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ማካሄድ አይቻልም የሚለው ፕሮፓጋንዳ የመድረክ ተመራጭ ስልት ሆኗል። በእኔ እምነት ገዥው ፓርቲ ለዴሞክራሲ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ብዙ ምክንያቶች አሉ። እነዚህም*

- *ኢህአዴግ በኢትጵዮያ የዴሞክራሲ አስፈላጊነት ላይ ሃገራዊ መግባባት በተፈጠረበት ወቅት የተመሰረተ ድርጅት ነው። አገሪቷን በመምራት ላይ ያሉት የኢህአዴግ መሪዎች ያኔ ወርቃማ የሆነውን ወጣትነታቸውን ጊዜ የሰውት ዴሞክራስያዊ የሆነች ኢትዮጵያን ለመመሰረት ነበር ። ከሁሉም በላይ ኢህአዴግ ይህን አላማ ለመተግበር እልፍ አእላፍ አባላቱን በመስዋእትነት ያጣ ድርጅት ነው። ስለዚህ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈለ ኢህአዴግን የመሰለ ድርጅት ለዴሞክረሲ ስርአት ያለው ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ አይችልም ።*
- *ኢትዮጵያ የተለያየ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አበቃቀል ያላቸው የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ነች። በዚህም ምክንያት አገሪቱ እንደ አገር መቆየት ካለባትም ሆነ አገሪቷ ውስጥ ትርጉም ያለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖማያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከተፈለገ በቅድሚያ የህዝቡን በጐ ፈቃድ ማግኘትን የግድ ይላል። ይህን የህዝቡን በጐ ፈቃድ ማግኛ ብቸኛው መንገድ ደግሞ ዴሞክራሲ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ዴሞክራሲን የግድ የሚልመሆኑን በሚገባ የተረዳው ኢህአዴግ ዴሞክራሲን በአገሪቷ ውስጥ ተግባራዊ እያደረገ ነው።*
- *የኢህአዴግ የፖለቲካ - ኢኮኖሚ ፕሮግራም የተቃኘው ከዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ጽንሰ ሃሳብ አኳያ ነው። ይህ ንድፈ ሃሳብ ደግሞ ዴሞክራሲና ልማትን በማቆራኘት ዴሞክራሲን የልማት ቅድመ ሁኔታ አድርጎ ያስቀምጣል። በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ይህ ንድፈ ሃሳብ ትርጉም የሚሰጠው ሃገራችን ያላት ኃብት መሬትና የሰው ጉልበት ብቻ በመሆኑ ነው። አጠቃላይ መነቃቃትን በመፍጠር የሰው ሃይልን አንቀሳቅሶ ፈጣንና ቀጣይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባትን መፍጠር ያስፈልጋል። አገራዊ መግባባትን የመፍጠሪያ ብቸኛው መንገድ ደግሞ ዲሞክራሲ ነው። ስለዚህ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባት ጠንክሮ እንዲሰራ የሚያደርገው የኢኮኖሚ ፕሮግራም ስላለው ለሥርዓቱ መገንባት ያለው ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚገባ አይዶለም።*

*ስለሆነም ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም እነዲሉ ሌትና ቀን መድረኩ ‘ ‘ኢህአዴግ ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ፍላጐት የለውም’ ’ በማለተ የሚያላዝነበት ፕሮፓጋንዳ ውሃ የማይቋጥርና አጠቃላይ ከሆነው የአገሪቱ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታ ጋርም የሚቃረን ነው የሚል እምነት አለኝ ።*